# ተቀምጠን የሰቀልነው ፀረ ኢትዮጵያ ዘረኝነት።ጃዋርን እዚህ ያደረሰው መንገድ

ዘወትር በዳያስፖራው ተቃዋሚ ክፍል እንደሚሆነው ጃዋር መሀመድ የተባለው ግለሰብ በ-አልጃዚራ ቴሌቪዥን የሰጠውን ፀረ ኢትዮጵያ አስተያየት መሰረት ያደረገ የተወሰነ ቁጣ አዘል የተቃውሞ ድምፅ ተሰምቷል። ፈረንጆቹ ሴሌክቲቭ አውትሬጅ የሚሉት አይነት። ለምን ይህን እንዳልኩ ለማስረዳት እሞክራለሁ። የጃዋር ፀረ ኢትዮጵያ ዘመቻ አዲስ ክስተት ሳይሆን ላለፉት ሀያ ሁለት አመታት በግልም ሆነ በድርጅት ሥልጣን ከያዘው ቡድን አንስቶ ራሳቸውን በተቃዋሚነት በፈረጁ ድርጅቶችም ጭምር የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው አጠቃላይ ዘመቻ አካል ነው። ጃዋርን ያስተዋወቁና የካቡት መድረክም የሰጡት ክፍሎች ድረ ገፆች/ሬድዮ/ቲቪ ማንነቱን ሳያውቁ አልነበረም በያዘው የጥላቻ ጎዳና እንዲነጉድ ያበረታቱት ስትራቴጂያዊ በሆነ መልኩ የወል ግብ ስላላቸው እንጂ።

ለማንኛውም  ቁምነገሩ ግለሰቡን  እዚህ ያደረሰውን ጉዞ መለስ ብሎ መመልከቱ ችግራችንን ከመሰረቱ ለመረዳትና (ሃያ አመታት እጅግ ብዙ ቢሆንም) ተገቢውን መፍትሄ መፈለጉ ላይ ነው። እግረ መንገዳችንንም ተቃውሞ ሲባል መርህን የተመረኮዘ እንጂ የምንደግፈው ድርጅት ወይም ግለሰብ ሲፈፅመው የምንቀበለው ጉዳይ መሆን እንደሌለበት ለማሳሰብም ነው። እስኪ ቀደም ሲል ጃዋርን መሰሎች የተፈጠሩበትን ወያኔያዊ ድልዳል ያመቻቹትን ሁኔታዎችና በህወሀት ጥላ ዋነኛውን ሚና የተጫወቱትን ግለሰቦች በጨረፍታ እንቃኝ።

ከወራት በፊት 'ሸገር' በተባለው ከሀገር ውስጥ በሚሰራጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ እንድርያስ እሸቴ የተባለው የሟቹ ወያኔ መሪ የመለስ አማካሪ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ከፐሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምና ክፍሌ ወዳጆ ከተባለው ሌላ የወያኔ ወኪል ጋር በመሆን በ1991 ለንደን ላይ ዩ ኤስ አሜሪካና እንግሊዞች ወያኔን ብቸኛ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ባስቻሉት ድርድር ላይ ኢህአፓና ኢድህቅን የመሰሉ ህብረ ብሔራዊ ድርጅቶች በሽግግሩ ላይ እንዳይሳተፉ ሀሳብ ማቅረባቸውንና ግፊት ማድረጋቸውን እንዳሰቡት እንደተሳካላቸውም ሳይደብቅ ተናግሯል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ሁሉም ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ይረዳዋል የሚል ግምት አለኝ። ፕሮፌሰሩ በዚህም ሳይወሰን ሻቢያ የፈጀውን ፈጅቶ የቀሩ ዜጎቻችንን የወርቅ ጥርስ ሳይቀር በቁመናቸው እያወለቀ ባባረረበትና የህዝባችን ልብ በቁጭትና በሀዘን በተመታበት ወቅት ለምን ኤርትራን እንደጎበኘና ፀረ ኢትዮጵያ ንግግር እንዳደረገ ሲጠየቅ ለመሆኑ ስንቱ ኢትዮጵያዊ ነው የወርቅ ጥርስ ያለው ሲል ጨካኝ ቀልድ ቀልዷል። ልሂቃኑ የወሰዱት አቋም የሀገርና ህዝብ የወደፊት እጣ ፈንታን በጭራሽ ግምት ውስጥ ያላስገባ ሀላፊነት የጎደለው ርምጃ ለመሆኑ ዛሬ ሀገርና ህዝብ ደም እያለቀሱ ያሉበት እውነታ ምሥክር ነው። የሚያሳዝነው ይህንኑ ተግባራቸውን ዛሬም በተለያየ ማደናገሪያ መቀጠላቸው ነው።

ፋሲል ናሆም የተባለው ደርግን በቅንነት ያገለገለ የህግ ፐሮፌሰር የወያኔ 'ህገ-መንግሥት' አርቃቂ ሲሆን የደርግ ህገ መንግሥት የእኩልነት መሰረት ነው ባለበት አፉ የወያኔን ህገ መንግሥት በምድር ላይ ተወዳዳሪ የሌለው ዕፁብ ድንቅ ሲሉ አሞካሽቶዋል። የአንዳንዶች ታቦት የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወያኔ ሥልጣን

ላይ እንዲደላደል የተቻላቸውን አድርገዋል። ‘መላ ወይስ ዱላ?’ በማለት ወያኔ ከፈቀደው ‘ሰላማዊ’ ከተባለው ልመና አይሉት ዘዴ ውጭ የሚደረግን ትግል በማጥላላት የፋኖነትን መንፈስ በመዋጋት ታላቅ የስነ ልቦና ሰለባ አከናውነዋል። ትውልድ ታሪኩን እንዳይወርስና ባለፈ ጀግንነት እንዳይኮራ ፋናውንም እንዳይከተል የቀዩን ሽብር የማሸማቀቅ ሚና አጠናክረው ገፍተውበታል። በመርማሪ ኮሚሽን የጀመረው የግፈኛ ሥርአት ባልደረባነት ታሪካቸው ዛሬም በሰላ መንገድ እንደቀጠለ ነው።  ታሪክ ይህን ሁሉ ይመዘግባል። ባሳለፍነው ሀያ ሁለት የወያኔ አመታት የትግልና ያርበኝነት መንፈስ ነውር ጉዳይ ተደርጎ በምትኩ ‘መቻቻል’ ና ‘ሥልጡን’ ፖለቲካ በተባለ ትርጉም አልባ ማደናገሪያ የትግል መንፈስ ተኮላሽቶ መጎንበስ ባህል እንዲሆን ከፍተኛ ዘመቻ ተካሂዷል። በዚህም አኳያ የተጠቀሱት ፕሮፌሰር ሚና ቀላል አልነበረም። ለህዝብና ለሀገር መቆም በቅድሚያ የሞራል ብቁነትን የሚጠይቅ ለመሆኑ በዚህ አኳያም የተመናመነው አቋማችን የተገዢነታችን አንዱ ምክንያትና መገለጫ ነው። አስመሳዩን ከሀቀኛው መለየት ስላቃተን። መለኪያ ሚዛን የጠፋበት ህብረተሰብ እንዳንሆን ያሰጋል። የአንድን የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ አቋም መመዘኛችን በውሸት የፈጠራ ታሪክ የተገነባ ድርሳን ሳይሆን ተጨባጭ ከሆነው የህዝባችን የዘመናት ምኞትና የሀገራችን ሉአላዊነት ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ መሆን ይኖርበታል። ከህዝባችን ፍላጎት በተፃራሪ ለቆሙ በህዝብ የመብት ጥያቄና በሀገር ህልውና ለሚደራደሩ ዕድል ልንሰጣቸው ወንጀላቸውን ልንታገስው በጭራሽ አይገባንም።

ጃዋር ወያኔ ፀንሶና ወልዶ ከላይ የተጠቀሱት ‘አይደፈሬዎች (untouchables)’ ኮትኩተው ባሳደጉት ዘረኛ ሥርአት አስተሳሰብ ያደገ በመሆኑ ሌሎች ያንን ካደረጉ እሱ ደግሞ እነሱ የሰጡትን ቢናገር ሊገርመን አይገባም። ከላይ የተጠቀሱትን በደሎች አይተን እንዳላየና እንዳልሰማ ካሳለፍን ያሁኑ ጬኸት እኛኑ ከማስገመት አያልፍም። ጬኸታችን አቅም አልባ የመሆኑም ምሥጢር ይኸው ነው። አባማን እያሞገስን ነፃ እንዲያወጣን’ ለሥልጣን እንዲያበቃን እየተማፀንን ‘ሱዛን ራይስ ላይ አራስ ነብር እንደሆንነው አይነት።

ህዝባችን ዘረኝነትን አንቅሮ የተፋው መሆኑን ቢያንስ የ 1997 ቱ ምርጫ ህያው ምሥክር ነው። ዘላለሙን ካድርባይነት የማይላቀቀውና በታሪክ አጋጣሚ ወደ ሥልጣን ከመጡ አምባገነን መንግሥታት ጋር በመቆም ከቀይ ሽብር እስከ በደኖ እስከ አሶሳ…የንፁሃንን ደም ያፈሰሰው ኦነግ የተወሰኑ መሪዎች የጥላቻ ፖለቲካ ቀኑ የጨለመበት መሆኑን በመረዳት ቀለማቸውን ሲቀይሩ እያየንም ነው። የችግር አሸንክታባቸው እንዳለ ሆኖ።

ዶር ጌታቸው በጋሻው የተባሉ ሌላ የ ግንቦት ተባባሪ ኦነግን በማዋደዱ ዘመቻ ወቅት መላው ኦሮሚኛ ተናጋሪ የኦነግ አባልና ደጋፊ ነው ሲሉ በድፍረት ተናግረዋል በመቀጠልም የአንድነት ሀይል ስለተዳከመና ኦነግም ጠንካራ ሀይል በመሆኑ ሥልጣን ሊይዝ ይገበዋል የሚል አሳፋሪ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። ዶሩ ለጥናታቸው ዋቢ ያደረጉት ‘ ከቤተሰቦቼ የኦነግ አባል ያልሆንኩት እኔ ብቻ ነኝ’  ሲል ገልፆልኛል ያሉትን አንድ የዘጠኝ አመት ልጅ ትረካ ነው። የኤኮኖሚክስ አስተማሪው አንድን ሀቅ የመረዳት መንገድ ይህ ከሆነ የሚገርም ነው።

በቅርቡ ያሬድ ጥበቡ የተባለው ወያኔ ናፋቂ ከሁለት ፕሮፌሰሮች ጋር ባደረገው ውይይት ጃዋር መሀመድ ዘመኑን የሚወክል አስተሳሰብ እያራመደ ነው የሚል ወኔያዊ ሀሳብ የሰነዘረ ሲሆን ከዚያም አልፎ በወያኔ አገልግሎት ዘመኑ የተነገረውን “ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም እኛ የምንሰራት ናት’ የሚለውን ሃሳብ በመድገም ኢትዮጲያዊነት የሚባል ሪያሊቲ መኖሩን እንደማይቀበል አስታውቋል። *

ግንቦት የተባለውም ድርጅት በብልጣብልጥነት የሞተውን ሌላ አካግ ነፍስ አዘርቶ ለማንቀሳቀስና የሆነ 'ታሪክ' ለመስራት ያደረገው ሴራ ከሽፎበት ባሁኑ ወቅት ከኢሳት ጀርባ እየተሽኮረመመ ይገኛል። ህቡእ ገባሁ እያለንም ነው። የግንቦት ሰባት መሪዎች የብሔር ድርጅቶችን ለማቅረብ በሚል ሽፋን ከወያኔ ባልተናነሰ ደረጃ በኢትዮጵያዊነትና በታሪካችን ላይ ከፍተኛ ዘመቻ አካሂደዋል።

አንዳርጋቸው ፅጌና ዶር ብርሃኑ ነጋ በይፋ ማይጨውና አድዋ የሀፍረት ታሪኮች ናቸው እስከማለት የደረሱ ሲሆን ሌላው የዚሁ ድርጅት የውጭ ጉዳይ ሀላፊ ኤፍሬም ማዴቦ በአፄ ምኒልክ ላይ ይህ ነው የማይባል የጥላቻ ዘመቻ አካሂዷል። የዚሁ ድርጅት መሪዎች የኢትዮጵያ አንድነት የተቃዋሚዎች ህብረት መሰረት መሆኑን አጥብቀው ይቃወማሉ በመሆኑም ተፈላጊው የድርጅቶች ህብረት እንዳይከሰት ታላቅ እንቅፋት ሆነዋል።የግንቦት ሰባት ጉዞና የተጨባጭ ሁኔታ ግምገማ በመካሄድ ላይ ላለው የተቃውሞ ትግል እጅግ ወሳኝ የሆነውን የኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎች የአንድነት ለመፍጠርና ትርጉም ያለው ትግል ለማካሄድ ታላቅ መሰናክል ሆኗል። ይህም ሁኔታ ማንን እንደጠቀመ ምሥጢር አይደለም። ማንኛውም ራሱን እንደ ኢትዮጵያዊ የሚመለከት ግለሰብም ሆነ ድርጅት የሀገሩን ህልውና በማንኛውም ፖለቲካዊ ሽፋን ለድርድር የማቅረብ መብት የለውም። ከዚህም በላይ የህዝባችን ምኞት (አስፒሬሽን) ማሳካት የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ሆነ ግለሰብ መሰረት ነው።

ታማኝ በየነ የተባለው የዚሁ ድርጅት አክቲቪስት አካግን ለማሻሻጥ በግንቦት ሰባት ከተካሄዱት ዘመቻዎች ባንዱ, 'በታሪክ ታስሮ መኖር የሰብአዊነት ምልክት አይደለም' ሲል ተፈላስፏል። ያለፈውን ታሪክ ማስታወስ አያስፈልግም ነው አባባሉ። የወትሮው ኩምክና ያለመሆኑ የሚገባው ግን ዘግይቶ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ሁሉ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር አንድ ጉዳይ ቢኖር በየድረ ገፁ ቋሚ አምድ ተሰጥቷቸው ባንድ አዳር በርካታ ገፆች ያላቸው መጣጥፎች የሚፅፉ ልሂቃን ፕሮፌሰሮች አንድም ጊዜ ይህን አንገብጋቢና አስፈሪም ጉዳይ ያላማንሳታቸው ሲሆን ባንፃሩ ከሶስት አሰርት በላይ ሌሎች ብዙ ያሉለትን ጉዳይ እንደ አዲስ መገለጥ (ለነሱ አዲስ ነውና) በስሜት እየፈነደቁ ነጋ ጠባ መደጋገማቸው ነው። ነገሩ ባይከፋም ወደ ዋናው ጉዳይ ያለመምጣታቸው ግን በራሱ ብዙ ይናገራል። አብዛኛው የተማረው ክፍል እስካሁን ያከናወነው ያለፉትን አፋኝ ሥርአቶች የፈጠራ ታሪክ ከመድገም ያለፈ የራሱን መለያ ማህተም በፖለቲካ ዲስኮርሱ ውስጥ ማሳረፍ ያለመቻሉ ወኔ ቢስነቱንና የደርጅቶች ጭራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። በዚህም የተነሳ የህብረተሰቡን አክብሮት ሳይሆን ትዝብት ብቻ ነው ያተረፈው።

እንግዲህ ጃዋርንም ሆነ መሰሎቹን የፀረ ኢትዮጵያዊ ዘረኝነት አላማ አራማጆችን አስተሳሰብ ስንቃወም ከላይ የተጠቀሱትን አይነቶች መሰል አጥፊዎችንም ያለርህራሄ ማጋለጥ ይገባል።

ዮሴፍ በሪ

ይቀጥላል።

ለተጨማሪ ንባብ።

**ኤፍሬም ማዴቦ፣** http://www.abugidainfo.com/index.php/18650/

ያሬድ ጥበቡ፣ http://www.awrambatimes.com/?p=9119